ፓኖራማ ቁጥር 78

<u>የትዝብት አድማስ</u>

መስከረም 16 ቀን 2002 ዓም

## <u>ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መሸጡን በፊርማ ሊያጸድቅ ነው</u>

ሰሞኑን አንድ የሱዳን መንግሥታዊ መግለጫ ይፋ እንዳደረገው ፥ ወያኔና የሱዳን ባለሥልጣኖች የሁለቱን ሀገሮች ወሰን ተካልሎ ለመስማማት በዝግጅት ላይ እንዳሉ ገልጿል ። ይህንን ስምምነት ተገባራዊ የሚያደርግም ፥ በሱዳን በኩል አንድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን የያዘ ኮሚቴ ተመስርቶ ሥራውን ጀመሯል ። የኮሚቴ አባሎችም፥የሱዳን የሀገር ግዛት ሚንስትር፥ የሱዳኑ ፕሬዝደንት አማካሪ፥ የሱዳን የመከላከያ ሚስትርና የሱዳን ውጭ ጉዳይ ምንስቴር ሚኒስትር ዶ. ኤታ ናቸው ። የሱዳን መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት በዚህ ኮሚቴ ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፥ ሱዳኖች ለወሰን መካለል ጉዳይ የቱን ያህል ከፍተኛ ዋጋ የሰጡት መሆናቸውን ይገልጻል ። ከዚህም በቀር ስማቸው በይፋ ያልተገለፀ በርካታ የኮሚቴ አባላት እንዳሉም ተነግሯል ። ሁኔታውን ለማጣደፍ በሙያው የተካኑ አባላትን የያዘ የቴክኒክ ኮሚቴም ተመስርቶ ሥራውን በማካናወን ላይ እንደሚገኝ ታውቋል። እንደ ሱዳን መንግሥት ይፋ መግለጫ ከሆነ፥ የወሰኑ መካለል ሥራ በሚቀጥለው የጥቅምት ወር ተጠናቅቆ መለስና ሱዳኖቹ እንደሚፈራረሙ ተብራርቷል ።በወያኔ በኩል ግን እስካሁን ድረስ ወያኔን ወክለው የተሰየሙት የኮሚቴ አባላት ስም ዝርዝር ቀርቶ፥ ስለ ድንበር መካለሉ እንኳን የተገለፀ ነገር የለም ። ምንም እንኳን እስካ ሁን ድረስ ወያኔ የኢትዮጵያን ለም መሬቶችና ስትራተጂያዊ ቦታዎች ለሱዳን አሳልፎ የሰጠ መሆኑን ተደጋግሞ የተገለፀ መሆኑ ቢታወቅም፥እናም ደግሞ ፥ በእኛ በኩል ተቃውሚችንን በየወቅቱ ማሰማታችን የተመዘገበ ቢሆንም ፥ይህ በሚመጣው የጥቅምት ወር በወያኔ የካሃዲ ጣት ይፈረማል የተባለለት የሀገር ሽያጭ ውል ፥ከሁመራ እስከ ወለጋ ግዛት የተንጣለለውን የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ሰፊ ግዛት በአደባባይ ለሱዳን የሚያስረክብ መርዘኛ፥ ጠንቀኛና አሳፋሪ ሰነድ ነው ። ነግ-ተነገ ወዲያ ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቀደድ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ሀገራችን ኢትዮጵያ በየአስር ዓመታት መሬቷን ለባዕዳን እንደልቡ የሚያስረክብ ቡድን ሲያጋጥማት በታሪኳ ይህ የመጀመሪያው ቢሆንም ፥ በዚህ ከሃዲ ዘረኛ ቡድን የተሸጠባትን መሬት የማስመለስ ህጋዊ መብቷ የተጠበቀ ነው ። ከሱዳን ጋር የሚያዋሰነውን የሀገራችን ለም የርሻ መሬትና ስትራተጂያዊ ቦታ ፥ ሱዳኖች አመች ናቸው በሚሏቸው አጋጣሚዎች ሁሉ፥ለመውሰድ ያደረጓቸው ሙከራዎች ሁሉ በቀደምት ብርቱ ዜጎቿ እንደከሸፈባቸው የታወቀ ነው ። በአፄው ዘመነ መንግሥትም የተለያዩ ሞከራዎች አድርገው ፥ በአካባቢ ነዋሪዎች ኢትዮጵያውያን ቆራጥ ተጋድሎ ሳይሳካላቸው ቀርቷል ። ከአንድ መቶ አስራ አንድ ዓመት በፊትም ፥ ሱዳኖች በውቅቱ ኢትዮጵያ በሌሎች ምዕራባውያን ቅኝ ገዥዎች መከበብና አደጋ ላይ መውደቅና የማዕከላዊው መንግሥትን መድከም ተገንዝበው ፥ በዘመኑ ኃያል ከነበረው ከኦቶማን ዓፄያዊ ግዛት በኩል መጠነ-ሰፊ የሆነ የጦር ርዳታ በማግኘት ወረራ አካሄደው ነበር።ይህም ወረራ የኣዕላፍ ኢትዮጵያውያንን ደም በጠየቀ መሥዋዕት ከሽፏል ። በአሁኑ ወቅትም ፥ ልክ እንደዚያኑ ዘመን የኢትዮጵያን መዳከምና ሀገራዊ ጥቅሟን ለመጠበቅም ሆነ የውጭን ኃይል ጥቃት ለመከላከል የሚችል

ብሔራዊ መንግሥት አለመኖሩን ተገንዝበው፥ ሱዳኖች ኢትዮጵያዊ ካልሆነው ኢትዮጵያዊ ቡድን ጋር የወሰን መካለሉን ጉዳይ ሌላ ጊዜ ሊገኝ የማይችል ወርቃማ ዕድል ሆኖላቸዋል ። ለጊዜውም ቢሆን ፥ደም-መላሽ የሌላት ኢትዮጵያም፥ይህን የወሰን መካለል ሂደት እንዲያው በደፈናው በዝምታ የምታልፈው ጉዳይ ከቶ ሊሆን አይችልም ። ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ጩኸቷን ሰምቶ ይደርስልኛል የምትለው ዓለም አቀፍ ተቋምም ይሁን ወገን ባይኖራትም ፥ ይህን ህገ-ወጥ ድርጊትና ጥቃት ዛሬ ሁሉም ዜጎቿ አጥብቀው የሚቀወሙ መሆናቸውን ታስመዘግባለች።

በእኛ በኩል ደግሞ ፥ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ልናስመዘግበው የምንሻው አንድ ነገር ቢኖር ፥ ይህ የወሰን መካለሉ ጉዳይ በዚህ ወቅት በሱዳን በኩል ይፋ የሆነው ፥ **" ሱዳን ያለምንም ገደብ ከያዘችው ከጎንደር መሬት በአስቸኳይ መውጣት አለባት "** ብለን መግለጫ ካወጣን አንድ ሳምንት በአልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑን ነው ። የወያኔንና የሱዳንን የቅርብ ግንኙነትና ፀረ-ኢትዮጵያ ትብብር በቅርብ ስለምንከታተል፥በእኛ ዕምነት፥ ይህ አሁን የሱዳን የወሰን መካለሉ ጉዳይ ፥ይፋ እንዲሆን መደረጉ ፥ እንዲያው በአጋጣሚ የሆነ ነው ለማለት እንቸገራለን ። በሌላ በኩል ደግሞ ፥ በከፊል የመንግሥት የሆነውና ሱዳን ትሪቢውን የተሰኘው የሱዳን ዕለታዊ የእግሊዝኛ ጋዜጣ ይህን የእኛን መግለጫ አስቀድሞ ማተሙም ያለምክንያት እንዳልነበር ለመረዳት አይቸግረንም ። የህገራችንን ብሔራዊ ጥቅም፥ የግዛት አንድነትንም ሆነ የሕዝባችንን የማይደፈር- የማይገሰሰ ነፃነት ለማስከበር እልህ አስጨራሽ ትግል ማድረጋችንን የሚገነዘቡ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይላት አሁንም በድጋሚ ሊገነዘቡት የሚገባው ቁም ነገር ቢኖር፥ መቸውንም ቢሆን በህገራችንና በሕዝባችን ላይ በመጣ ጉዳይ ቀናዒ መሆናችንን ነው።ያለ ጥርጥር ከሃዲያን ከሱዳን ጋር የሚፈራረሙት የወሰን ክልል ነገ በዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ ድንበሩ ይፈልሳል ። ውሉም ይሻራል ። ፊርማውም ይቀደዳል ። የተሸጠው መሬትም ወደ አባት-አደሩ ይመለሳል ። ይህ ሀቅ ደግሞ ፥ እንዲያው ኢትዮጵያ አንድያዋን፥ጠፍታ፥ ከስማ ፥ ዜጎቿም እንደ ጨው ዘር ሟሙተው ካልከሰሙ በቀር ፥ እንደሚረጋገጥ ፥ ኢትዮጵያዊው ሁሉ ያምንበታል።ይህንን ጉዳይ ህያው ለማድረግ የሚኖረው ምርጫ ደግሞ አንድ ብቻ እንደሆነ የታወቀ ነው ። የህገራችንን መሬት ለሱዳን ፈርሞ ያስረከበው የወያኔ ቡድን ፥ ከሥልጣኑ ኮረቻ መውረድ ይኖርበታል ።ይህ ካልሆነ ፥ የኢትዮጵያን ምዕራባዊው ክፍል እንደሸጠው ሁሉ ፥ አመች ጊዜ እየጠበቀ ፥ ሌሎቹንም የህገሪቱ ወሰኖች የመቸብቸብ ሥራውን እንደሚቀጥልበት መጠርጠር አይቻልም።

በመሠረቱ፥ ወያኔ የህገሪቱን ድንበር አስመልክቶ፥ ከማነኛቸውም የጉረቤት ሀገሮች ጋር ለመደራደርም ይሁን ለመካለል የሚያስችለው፥ የታሪክ ተልዕኮም ይሁን ፥ ህጋዊ ምርጉዝ ወይም የፖለቲካ ሥልጣን ሊኖረው ከቶ የሚችል ቡድን አይደለም ። እንኳንስ የመላዋን ኢትዮጵያ ወሰኖች ቀርቶ ፥ እወክለዋለሁ የሚለውን የትግራይንም ክፍለ ሀገር መሬት ሊያሰፋም ሆነ ሊያጠብብ የሚያስችል ህጋዊ ውክልና የሚኖረው አካል አይደለም።የታሪክም ሆነ የፖለቲካ ሥልጣን ወይም ደግሞ የሞራል ልዕልና ይኖረኛል ብሎ ሊል የማይችልበት ምክንያቶች በርካታ ናቸው ። ከእንኝህም ውስጥ፥ ዋና ዋናዎቹን እንጠቅሳለን።

1ኛ. የኢትዮጵያን ድንበር ለማስከበር መተማ ላይ የፈሰሰውን የኢትዮጵያውያንን ቅዱስ ደም ታኩሪ በማርከሱ ነው ። የዛሬውን የወያኔን ክህደት መመልከት ቢችሉ፣ አፄ ዮሐንስ ራባኣይ የተከበረው አፅም ከመቃብራቸው ውስጥ ሆኖ ይገላበጥ ነበር ። ወያኔ መተማና ገላባት ላይ የተከሰከሰውን የጀግኖቻችንን የተከበረ አጽም ረግጦና ተራምዶ ካርቱም ላይ ከነበሽር ጋር ተሻርኮ የኢትዮጵያን መሬት በፊርማው ለማስረከብ በመሞከሩ ፥ ኢትዮጵያዊ ታሪክ የመልበስ ብቃቱ ተገፍፎበታል ። በትውልድና በዜግነት ኢትዮጵያዊ ቢሆንም፥ ወያኔ ርጉም ልጅ ስለሆነ ኢትዮጲያዊ ዜግነቱን እርሱ ራሱ በገዛ እጁ አርክሶታል።

2ኛ. ወደ ሥልጣን ሊመጣ የቻለውም በኢትዮጵያ የቅርብና የሩቅ ጠላቶች ትብብርና ውሳኔ በመሆኑ÷ የባዕዳንን ጥቅም እያስጠበቀ ያለ የወገን ባዕድ ሆኗል:: በመሆኑም÷ የባዕዳን አስጠባቂ ቡድን በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ ምርጉዝ ሊኖረው አይችልም::

3ኛ. በዘር ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ሥርዓት ዘርግቶ ÷ የአምባገነን አገዛዝ በማካሄድ የዜጎቻችን ዴሞክራሲያዊ መብት ያፈነ ቡድን ÷ የፖለቲካ ሥልጣን ልዕልናም ይሁን ሕዝባዊ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ÷የሚዋዋላቸው ውሎች÷ ስምምነቶችና ፊርማዎች ዋጋ አይኖራቸውም::

በነኙህና በሌሎችም መሠረታዊ በመሆኑ ምክንያቶች÷ ወያኔወቹ÷ ታሪካዊ ተልዕኮ÷ ህጋዊ የመከራከሪያ ነጥቦችና የፖለቲካ ሥልጣን ስለ ሌላቸው ይህ በመጭው ጥቅምት ወር ሁለት ሽህ ሁለት (2002) ዓም ከሱዳን ጋር ሊፈራረሙ ሽር ጉድ የሚሉት የድንበር ስምምነትና ውል÷ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኩል ተቀባይ እንደማይኖረው መታወቅ አለበት:: እኛም ይህኑ እናስተጋባለን:: የወያኔን የሀገር መሸጥ ክህደት እንቃወማለን:: እናወግዛለን :: ሌሎች ሀገር ወዳድ ዜጎችና ተቀዋሚ ኃይላት በየበኩላቸው ድርጊቱን አውግዘው ተቀውሟቸውን እንዲገልጹና እንዲያስመዘግቡ ጥሪያችንን እናስተላለፋለን !